ሐዋርያ

ልዩ

ዕትም

# ያ ትውልድ የቤት ሥራውን ያጠናቅቅ

በህይወት ሂደት ላይ ዳግም ላይመለሱ ደርሰው አልፈዋል ተብለው የሚገመቱ አንዳንድ መልካም ሁነኛ ኩነቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ ጊዜና ዘመን ላይ ድንገት ቦግ ብለው ሲከሰቱ፤ በህይወት የመኖር ትሩፋትን በአንክሮ ለማጤን ይረዳ ዘንድ “መሮር መስታወት ነው” ይባላል። እንዲህም ሆነና ዛሬ በሀገራችን ውስጥ ገዝፎ የሚታየውን ሕዝባዊ የፖለቲካ ነውጥ ከ1966ቱ የየካቲት ሕዝባዊ አብዮትና በዚያ ዘመን ሙሉ ሃላፊነት ወስዶ በትግሉ ማእበል ውስጥ ከተርመጠመጠው ፋና ወጊ ትውልድ ጋር በተመሰጠ ልቦና አዛምደን ስንዘከር በእርግጥም ይህ እንዲሆን ምናባችን ሲናፍቀው ኖሯልና በገቢር ተፈጽሞ ስናይ የጊዜን ጥበበ-ሥራና እንደ ንጹህ መስታወት ሁሉን የማሳየት ሃቁን እናረጋግጣለን። ያን ጊዜ፤ በዚያን ዘመን ከዕለታት አንድ ቀን በአንዱ ማዕልት በወቅቱ ተራማጅ ከነበሩት እትሞች አንዷ - የኢሕአፓ ልሳን የሆነችው ዴሞክራሲያ- አንገብጋቢ የትግል ጥሪ መልእክቷን ተሸክማ በኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ተሰራጭታ አደረች ተብሎ ተነግሯል። በዘመናት በደልና ግፍ ተማሮና ተሸማቆ ይኖር የነበረው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተስፋ ገላጯ ቀዳማይ ዴሞክራሲያ ትግል ጥሪ ከረዥሙ የአርምሞ ትግሉ ቀና እንዲልና ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ በታላቅ ተስፋ ትግሉን ደግፎ እንዲቆም ሆነ፤ የሀገሪቱ አየር ከትግል ስሜት በነተበ ማዕዛ ዳር እስከ ዳር ታወደ። የዚያን ዘመኑ ብርቅዬ ወጣት ትውልድ እናት ሀገሩን በጋራ አስቦ፤ ሁላችንም እኩል የአንዲት ሀገር ልጆች ነን፡ እየተበደለ ያለውም የሁላችን ወገን ነው በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሟላ መብት መከበር ሲል፡ ፍትህ ርትእ እውን እንዲሆን በመሻት ለብሄር/ብሄረሰቦች መብት መከበርና እኩልነት ሲባል… ትግሉን ‘ሱብ’ ብሎ በመጀመር የውሎ በሬ ሆኖ ተጠመደ።

ተቀጣጥሎ በቀጠለው ወኔ ፈታኝ ሕዝባዊ ትግል ውስጥ የሳት ረመጥና ትንታግ በመሆን ለአንዲት ህይወቱ አንዳችም ሳይሳሳላት አምባገነኖችን በግንባር ቀደምትነት ተጋፈጠ። እንደ አንድ አዲስና አደራ ተረካቢ ትውልድ በግፍና በበደል ላይ አምጾ በጭቆና ሥር የወደቀውን ሕዝብ ነጻ ማውጣትና የራሱን ብሩህ ተስፋ ማብራት የሚያኮራውና የሚያስከብረው ጀብዱ፡ የማያልፈው የአደራ ተቀባይነት ዕዳው አድርጎ ወሰደው። የሀገሪቱ ወጣት ልጆች አንድም ሳይለያዩ፤ በቀለም በቋንቋ ላንዴም ሳይተሳሰቡ፤ የዘርና የሃይማኖት ልዩነትን ለትግላቸው ስሌት ሳያውሉ፤ እናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ከተሟላ የልጆቿ መብትና እኩልነት ጋር በዕድገት

ጎዳና ላይ የምትውልበትን ህልም ሰንቀው ተሰለፉ። ማህበራዊ የሽግግር ለውጦች ሁሌም እንደሚያሳዩት፡ ይህ ሕዝባዊና ሀገራዊ ራዕይ በሥልጣን ለሰከሩ አምባገነኖች አይመችም ነበርና በተከተሉት ዓመታት ውስጥ ያ ብሩህ ወጣት በጨካኞች ጥይት ተቆላ፤ በስይል ተሰቃይቶ ደነዘዘ። መሬት ለአራሹ እንዲሆን በጠየቀ፡ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ መብትና እኩልነት፡ ብሎም ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት በጠየቀ ትውልድ ላይ መዓት ወረደ፤ እናት ከል ለበሰች። በዚህም በሕዝብ ልብ ውስጥ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦምብ ተቀበረና ጊዜው ሲደርስ ጭካኔያቸው ዘላለማዊ ያስመሰላቸውን አምባገነኖች አዳፍኖ ሲቀብራቸው ሌላ ጊዜ ላይ ሆነን በሌላ የጊዜ መስታወት ተመልክተነዋል።

ያ በየካቲት 1966 ዓ.ም የተለኮሰው ሕዝባዊ አብዮት በወረደበት ዶፍ ምክንያትና በውስጡ በተወለዱ ልዩ ልዩ አሳዛኝ ጦሶች ተዳኮሞ በመዛሉና ትግሉን በራሱ አቅምና አቅጣጫ ማከናወን ባለመቻሉ ዕድሉን ጊዜ ላጋጠማቸው ቀማኞች አሳልፎ ሰጥቶት ቆይቷል። ይሁን እንጅ ያ ትውልድ በአሁኑ ሰዓት እንደልጅነቱ እየነደደ ሲቀጥጥ በጉልህ ባይታይም በያለበት የተዳፈነ ፍም ሆኖ እያሞቀ መግጠሙን ግን ከቶውንም አቁሟል አይባልም። አመድ ቢለብስ አመድ የሆነ መስሏቸው ተራምደውት ላለፉና ክፍፍልን እንደጥበብ ለሚጠቀሙ የዘመናችን ከይሲዎች የማይጠግግ የህሊና ቁስል እንደሆነባቸው አለ። አብዛኞቹ የዚያ ትውልድ አባላት በያሉበት ልዩ ልዩ ተቋሞችን በመፍጠርና በሕዝቡ መካከል በመገኘት አጋጣሚን እየተጠቀሙ የዘላቂ ሃሳብና መፍትሄ አውታሮች በመሆን ታግለዋል፡፡ ባረመመው ትግላቸውም የበሰለ ግንዛቤያቸውን መሪ አድርገው ሴረኞች የቋጠሩትን እየፈቱ፡ የበተኑትን እየሰበሰቡ በትግሉ ሂደት ውስጥ የህይወት ስትንፋስ ሆነው ኖረዋል። ትውልዱ በተዘመተበት የጥፋት አዋጅ እንዳይጠፋም ልጆቻቸውን በሕዝባዊና ሀገራዊ መንፈስ ማሳደግ ግዴታ ነውና እነሆ ዛሬ ዘርተው ያፈራውን እያፈሱ ነው። ህልማቸው አልሞተም፤ ይልቁንስ አመድ ለብሶ ከተዳፈነበት ምድጃ ከያለበት ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ገጦ ለተቀጣተለው እሳት ቤንዚን ሆኖ አያይዞታል። ከዚያ በጎ አሳቢና እልኸኛ ትውልድ አብራክ ተወልደው የአባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ትኩስና ጣፋጭ የትግል ታሪክ እየተመገቡ ያደጉ ወጣቶች፤ ያ ትውልድ በዘራበት ለም ማሳ ላይ የበቀሉ እምቡጦች፡ ዛሬ አብበውና ፈንድቀው በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በመነስነስ ሙሉ ኢትዮጵያን በማዕዛቸው እየሠረከቱ ነው። ታዲያ እድሜ ተርፎት በትርፍ ጊዜው ውስጥ የሚኖር የዚያ ትውልድ አካል የሆነና በኢሕአፓ የትግል ታሪክ ወይም በሌሎች ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ተወልዶ ያለፈና የኖረ፡ የወጣትነት ዘመኑን በትግል በመከራ አሳልፎ እንዳሰበው ሳይሆን ቀርቶ በትካዜ እንጉርጉሮ ያዘግም የነበር ደንገጡር ትውልድ፡ ዛሬ ምን ይሰማው ይሆን ብሎ ማሰብ ብቻ ሳይሆን፤ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ በቀረቺው ጥቂት ጊዜ ውስጥ ምን ማድረግ አለበት የሚል አንገብጋቢ ጥያቄ ማንሳትም ተገቢ ይሆናል።

በህይወት ያሉ የዚያ ትውልድ አባላት ሲታገሉ ከወደቁ ሙታን ጓዶቻቸው ጋር ሆነው የጀመሩትን እንዲጨርሱ ታሪክ ዛሬም እንደገና ሌላ እድል ሰጥታቸዋለች። በዚያ ትውልድ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግንዛቤ ያለፉ ዜጎች የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ እምቢተኝነት መስመር ይዞ እንዲተምና ወደ ዘላቂ ግብ እንዲያነጻጽር አጣዳፊ መልስ ይሰጡ ዘንድ ወቅቱ በያሉበት ንቁጣ የግድ ይላቸዋል። ለሙብቱ በተነሳሳው ሕዝብ ውስጥ ቢያንስ በየግላቸው ተሰልፈው ሰፊ ባህር ሃሳባቸውን በሥራ ላይ የማዋል አጋጣሚ ያገኙ ሲሆን፤ በሌላ በኩልም በትግሉ ጎራ በግንባር ቀደምትነት ለተሰለፉት ልጆቻቸው በየቤታቸው ትጉህ አማካሪዎች ሆነው መገኘት ሊጠበቅባቸው ይችላል። ለዘላቂው መፍትሄ ደግሞ ትውልዱን ዳግም ላያስቡትና ላይመለሱ ከሸሹትና ከወጉት በመለስ ድርጅታዊ እንቅስቃሴን አስቀጥለው በትግል ላይ ካሉት ወገኖች ጋር ፈጣን ግንኙነት እየፈጠሩ ንጹህ ውይይት በመጀመር ጊዜና ቦታ መርጠው አጠቃላይ የመልሶ

መጠናከሪያ ጉባኤ ማካሄድና ለሀገሪቱ አንድ ጠንካራ አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲ ማመቻቸት የረጅሙ ትግል መሰብሰቢያና ማሰሪያ ይሆናል ብሎ መተንበይ ይቻላል። ያ ትውልድ ሲባል በአብዛኛው የኢሕአፓ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የተንጸባረቀበት ቢሆንም በየፈርጁ የነበሩትን ሌሎች ዴሞክራሲያዊና ግራ ዘመም እንቅስቃሲዎችንና በቀናኢነት ለሀገራቸውና ለወገናቸው ጥቅም ሲሉ በያሉበት ሁኔታና አመለካከት ውስጥ ሆነው ያሰቡትን ሁሉ ያጠቃልላል። ኢትዮጵያንና ሕዝቧን አስበው እስከተንቀሳቀሱ ድረስ ልማቱም ሆነ ጥፋቱ  እንደ ትውልድ ይመለከታቸዋልና እንዲህ ሁኔታው ሲጠይቅና ሕዝባችን ሲጣራ ባለፈው ድክመት ታርሞና ተምሮ ትግሉን ከግብ ለማድረስ መቀራረብና መተባበር ይኖርባቸዋል። ያን ትውልድ የማይበጠስ የታሪክ ግማድ አተሳስሮታል። በለማውም ይሁን በጠፋው ነገር ሁሉ ትግሉ ግብ እስካልመታ ድረስ ሃላፊነቱን ታሪክ የግድ ያሸክመዋል። እስከዛሬ የቀጠለውን የፖለቲካ ሂደት ያነሳውና የቆሰቆሰው እሱ ነውና፤ በዓላማውም ብዙዎቹ አምነው ተቀብለው ተሰውተውለታልና፡ ሀገርን ከውድቀት ለማዳን ራሱን መልሶ አጠናክሮና ከልጆቹ ጎን ተሰልፎ በመታገል ታሪኩን በድል ህያው ማድረግ ይጠበቅበታል። ምን ጊዜም የእርስ በርስ ፍቅርና ትዝታው ያልተለያቸው የዚያ ትውልድ አባላት ዛሬ ወርቅ ጊዜ እጃቸው ውስጥ ይንከባለላል፤ ሊጨብጡትና ሊከውኑት ከወሰኑ ሌላ እድል አጋጥሟቸዋል።

በየትም ቦታ ያሉ የዚያ ትውልድ አባላት አብዛኞቹ ዛሬም ድረስ የልጅነት ተጋድሏቸውን አንስተው አይጥግቡትም። ሕዝባዊ ፍቅራቸውና ተቆርቋሪነታቸው እንደታተመ ያለ ለመሆኑ ማስረጃ ከሚሆኑት ብዙ ክስተቶች አንዱ በውጭ ሀገር ላለፉት 33 ዓመታት በየዓመቱ በሚካሄደው የኢትዮጵያዊያን የሰሜን አሜሪካ ስፖርት ሳምንታዊ በዓል ላይ የኢሕአፓ የድሮ አባላት ላንዴም ሳያቋርጡ በየዓመቱ የሚያደርጉትን ናፍቆታዊ ግንኙነትና የሃሳብ ልውውጥን  መመልከት ይበቃል። በዘንድሮው ቶርንቶ፤ ካናዳ በተከናወነው የስፖርት በዓል ወቅት ዘመን አመጣሽ ዘርና ጎሣ ሳይለያቸው ከተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶችና ከካናዳ የመጡ የድሮ የፓርቲው አባላት ባደረጉት የግንኙነት ምሽት ላይ የታዘብነውም ይኸውን ናፍቆታዊ ስሜት ነው። በትግሉ ወቅት ለወደቁ ጓዶቻችው የህሊና ጸሎት ሲያበረክቱ፤ ያለፉበትን ታሪክ ሲዘከሩ ተመልክተናል። ልባቸው ውስጥ ሕዝባቸውና እናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ እንደተነዘነዙ አሉ።

በዚያ ትውልድ የትግል ታሪክ ውስጥ ማለፍ ሲታወስ ለባለታሪኮቹ ብዙ ነገሮች ገዝፈው ሊታይዋቸው ይችላሉ። በኢሕአፓ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ዙሪያ እትብታቸው ላልተቆረጠና ተወልደው ላላደጉበት፤ እንደዚሁም ዘግየት ብለው ለተከተሉና ለሚተኩ አዳዲስ ትውልዶች ስለኢሕአፓ የሚወሳ ትረካ ሁሉ የፈጠራ ፊልም ሊመስላቸው ይችል ይሆናል፤ የኢሕአፓ አነሳስና በኩራዊ እርምጃ እጅግም አስደናቂ ነበርና እንዲያ በሚያስቡ ወገኖች ላይ መፍረድ ያስቸግራል። አንድ ትውልድ ነፍስና ሥጋውን አዋህዶ እንደ ጅረት በአንድ መስመር የፈሰሰበት ግብዓት ነበርና በዛሬው ውጥንቅጡ የወጣ የፖለቲካ ዕይታና ስሌት ሲመዘን አንድም ፈጠራ አሊያም ቅዠት ሊመስል ይችላል። ሃቁ ግን በተግባር የተዳወረና አንድ ትውልድ ለኖረበት ዘመን ሙሉ ሃላፊነት በመውሰድ መለያው አድርጎ ያሠረው የታሪኩ ክታብ ነው። የኢሕአፓ ትግል ታርክ እንደዛሬዎቹ ብዛታቸው ሥንክሳር የሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ትግል አየር በአየር የከነፈና በስሜትና በተቆርቋሪነት ብቻ፤ ወይም ደግሞ በተክለ ሰውነት ላይ የተንተለጠለና የተመዘነ ሳይሆን አባላቱ በየዕለቱ በቀጣይነት እንደ ቆሎ ተማሪ አንገታቸውን ቀብረው የረቀቀ ንድፈ-ሃሳብ አጥንተውና የግድ በሆነ የአሃድ ውይይት ዳውረውና አዳብረው በጠጣር ዲሲፕሊን ያንቀሳቀሱት የሕዝብ ትግል ነው።

ዋናው ነገር መጨረሻው ምን ሆነ፤ ወይም ምን ይሆናል የሚለው ነው። ካለፉት አምሳ ዓመታት ጀምሮ የተምዘገዘገውና ገና በደማና ውስጥ አየር የሚቀዝፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፖለቲካዊ ትግል የተለኮሰው

በዚያ ትውልድ አብሪነት መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህም፤ በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ ያን ከባድ ሃላፊነት የወሰደ አባወራ ትውልድ  ቃሉን ጠብቆ የት ላይ እንደደረሰና እንዳደረሰን መጠየቅ አግባብነት ያለው ይሆናል። አባቶቹና እናቶቹ ከጎደሎዋ ጋር ክብሯን እስከነወዟ ጠብቀው ያስረከቡትን እናት ሀገሩን እበልጣለሁ፡ እልቃለሁ ብሎ ከእጃቸው ሞልቅቆ ለተረከባት ታሪካዊ ሀገር እስከዛሬም ድረስ ለማይበገር ልዕልናዋና የላቀ እድገቷ እየተሟሟተላት መሆን አለመሆኑ በእርግጥም መጠየቅና መልስ መስጠት ያለበት ትውልድ ነው። የተጓዘበት ጎዳናና ያጋጠመው መሰንናከል  እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም፤ የሀገርን፡ የታሪክን፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሕዝብን የወደፊት ዕድል በወሳኝነት ቀልሞ የተረከበው ሃላፊነት እንደተራ ጨዋታ ታይቶ አይታለፍምና ያ ትውልድ የት አለ ተብሎ መፈለግና ሂሳቡን እንዲያወራርድ መጥሪያ ማስገባቱ አግባብነት አለው። ለሀገሪቱ የወደፊትት ዕጣ-ፋንታና ወዶ ደግፎት ለነበረ ሰፊ ሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን እዳር ማድረስ ይችል ዘንድ አዲሱን የሀገራችን ሁኔታ ብስለት በመላበት መንገድ ሊቀበለው ይገባል። ይህ ካልሆነ ያ ትውልድ በጅምሩ ወቅት በወሰድው ፈጣን እርምጃ የተወደሰውንና የተወደደውን ያህል ሀገሪቷና ሕዝቧ መጨረሻ ላይ በሚጋቱት ውድቀት ምክንያት የታሪካችን መርገምና የከፉ ዘመን ትውልድ ማስታዎሻ እንዳይሆን ሊታሰብበት ይገባል። መሆን የማይገባው ከሆነ ደግሞ ከታሪክ ተወቃሽነት የሚያመልጥ ማንም ስለሌለ እጣት መቀሳሰሩ ነጻ አያወጣም።

እንደ ድርጅቱ ትልቅነትና ሚና ኢሕአፓን በየደረጃው በሃላፊነት መርተናል ወይም እንመራለን የሚሉ ወገኖች ለትግሉ መርገብና አልባሌነት ትልቁን የዝሆን ድርሻ ይጋራሉ ተብሎ ሊታመን ይችል ይሆናል። ይህ የታሪክ ሃላፊነት የሚያስደነግጣቸው ካሉ፤ የዚያ ህልመኛ ትውልድ መሪ የነበሩና የሆኑ አባቶችንና እናቶችን ሕዝባችን ዛሬም ከመቸውምጊዜ በበለጠ ይፈልጓቸዋልና አስበውበት ከፈጠኑ እዳቸውን ሊወጡ ይችላሉ። እየመሸ ነውና ፀሐይ ሳትጠልቅ የሆነውን ሁሉ ለታሪክ ትተው እርስ በርሳቸው በይቅርታ ከተጎናበሱ፤ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ባደረገና ዓለም አቀፍ ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ ድርጅታቸውን ኢሕአፓን ከሰመመን እንቅልፍ መቀስቀስ ከቻሉ ከታሰበው የሚያደርስ በቂ ጊዜ አለ። ይህ ደግሞ ይቻላል፤ "አጥፍተን ልንጠፋ ነው" የሚል አስደንጋጭ ገጣጣ ስሜት የታሪኩን ባለቤቶች ከቀሰቀሰ፤ የዚያን ትውልድ ጥያቄዎች ለመመለስ ጊዜው ከመቸውም በበለጠ አመች ነው። ገና በጥዋቱ ኢሕአፓ ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች በአሁኑ ጊዜ የበለጠ ነጥረውና ጎልተው ቢታዩ እንጅ ተድበስብሰው ሚዛናቸውን አልቀነሱም። ኢሕአፓ አሳዛኝና አስተዛዛቢ ከሆነው የውስጥ ችግሩ በመለስ በሕዝብ ዘንድ የታዘነበት ጉዳይ ቢኖር ልጆቻችን በፍቅር ጠልዝዘውየ ሞቱለት ዓላማ ፍሬው አልታየም በሚል ቁጭት እንጅ በመሠረታዊና መተክላዊ አቋሞቹ ማንም እስከዛሬ ሞግቶ የረታው፡ ታግሎ መሬት ያስነካው የለም። በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ አንድነት መታገሉ፤ ዴሞክራሲያዊ መብትን ለሁሉም መስበኩ፤ መሬትን ለአራሹን መጠየቁ፤ የተከበረችና ያደገች ኢትዮጵያን መሻቱ፡ በሕዝብና በሀገር ጥቅም ላይ አለመሞዳሞዱና አለመደራደሩ - ለዚህም የሀገሪቱን ልጆች ዳር እስከዳር አስተባብሮ መትመሙ- ምንጊዜም በሕዝብ ዘንድ የሚያስከብረው እንጅ ዝቅ ተደርጎ የሚታይበት አይደለም።

አሁን በምንገኝበት አስቸጋሪ  የሀገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ በሕዝባችን ዘንድ ለመፍትሄ አሰጣጥ ሊሰሙና ሊደመጡ ከሚችሉቱ መካከል ኢሕአፓ አንዱ ሊሆን ሲችል፤ ለመታመንና አደራ ለመቀበል የሞራል ብቃት ካላቸው እንቃቃሴዎች መካከል ደግሞ ቅድሚያውን ይይዛል ቢባል ከንቱ ኩሸት አይሆንም። ይህ ደግሞ አሁን ለምንግኝበት ሕዝባዊ እምቢተኝነትና የሽግግር ወቅት የዚያ ትውልድ ተሳትፎ ላቅ ያለ እሴት መሆኑ ነው። ለሃያ አምስት ዓመታት በክፍፍል መርዝ አሳሩን ያየ ሕዝባችን፡ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ስም እየመጡና እየሄዱ ብዙዎች የተጫዎቱበት ኩሩው ሕዝባችን፡ ሁሉንም አይቶ

መታዘቡ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ባለው ወሳኝ ውቅት ላይ የእኔ ብሎ የሚያምነውና የሚወግነው ሃይል ይፈልጋል። ኢሕአፓ የአብዛኛው ተራማጅ ኢትዮጵያዊ ቤት ነበርና፤ አሁንም ለሕዝባዊነቱ የተለወጠ መተከላዊ ማስተካከያ ስለሌለ ለሁሉም ይቆረቆራል፡ ይታገላል ተብሎ ሊታመን የሚችል ነው። አገራችን ለህልውናዋ መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች በምትባልበት በአሁኑ ወቅት፡ በሥልጣኑ ላይ የበሰበሰው ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ከሰፊው ወገናቸው ነጥሎ እያስጠቃቸው ያሉትን የትግራይ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን፡ እንዲሁም የእርኩስ አላማው መተግበሪያ ያደረገውን ሠራዊቱን ከሕወሓት መንጋጋ በሞራል ብቃትና ሀገራዊ ፍቅር መንጠቆ በማላቀቅ ሀገሪቱን ከሁለገብ ጥፋት መታደግ የሚቻልበት አንዱ መንገድ በኢሕአፓ በኩል ተሠርቶ በቆየው ድልድይ ላይ ነው ብሎ ማመን ይገባል። እንደሌላው የሕዝብ ክፍል ሁሉ የትግራይ ሕዝብ ኢሕአፓን በፖለቲካ አባዎራነቱ በቅርብ አሳምሮ ያውቀዋል፤ ያከብረዋልም። እናም አሁን በምንገኝበት ቀውጢ ጊዜ ውስጥ ኢሕአፓ ሲጣራው አቤት ሊለውና መልስ ሊሰጠው እንደሚችል ይገመታል። በዚህም ሀገራችን ከውድቀት፡ ሕዝባችን ከከፉ የታሪክ ጠባሳነት እናድናለን። የኦሮሚያን፤ ጎንደርን፤ ጎጃምን፤ ሸዋንና የተለያዩትን ብሄረሰቦችና አካባቢዎች ልብ ለልብ የተገናኘ ሕዝባዊ እምቢታ ስንመለከት፡ እንግዲህ በሁዋላ ከፋፋዮችንና አምባገነኖችን ማንም አይፈራም። የሚያስፈራ ሌላ ነገር ግን አለ - ለሃያ አምስት ዓመታት የተነሰነሰው የከፍፍል መርዝ ማሻሪያ ጥበብ ይሻዋል። እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ ትግል መደገፍና መበረታታት ያለበት ሆኖ፤ ነገር ግን ሁሉንም አቀናጅቶ ወደ ሀገራዊ ሥርዓት ምሥረታ የሚመራ ታማኝ አካል ከሌለና ሁሉም በየአቅጣጫው በመሄድ ከደነደነ አፋኙ ሥርዓት ሲያከትም አንድወጥ ሀገር ማደላደልና ማቆም እንዳይቸግር ልብ ሊባል ይገባል። የዚያ ትውልድ አባቶች፡ በተለይም የኢሕአፓን ታሪክ የተላበሱ እናቶችና አባቶች ለአንዴም ለመጨረሻም በይቅርታ ጸበል ተፈውሰው ለሕዝባችን ይድረሱለት የሚያሰኘውም ይህ አይነቱ ስጋት ነው። እያኮራን የሚገኘው አዲስ ትውልድም በእንዲህ አይነቱ የቀደምቱ ትውልድ ሥምሪትና ሃላፊነት ከአባቶቸና እናቶቸ የተረከብኩት አደራ ብሎ እንዲመካብን እድል ሊሰጠው ይገባል። ∞